የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም
April 27, 2015

# የላብ-አደሮችን ቀን (ሜይ ዴይ) ዛሬም እናከብራለን

በየዓመቱ በፈረንጆች አቆጣጠር ሜይ አንድ ቀን የሚከበረው የሠራተኞች ቀን ላብ-አደሮች የሚያደርጉትን ትግልና ለኅብረተሰቡ ያደረጉትን አስተዋጽዖ እንዲሁም ወደፊት የሚጠብቋቸውን ተግዳሮቶች ለመዘከር ነው። የበዓሉ አከባበር የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለዘመን በምዕራቡ ዓለም ላብ-አደሮች ግምባር ቀደምትነት ሲሆን፣ ዓላማውም ለመሠረታዊ የሠራተኛው መብቶች ተፈጻሚነት ነበር። እነዚህም በአግባቡና ሰብዓዊ በሆነ መልኩ የአንድን ቤተሰብ የዕለት ተዕለት ወጪ ሊሸፍን የሚያስችል ክፍያ ለማስገኘትና ለሠራተኛው ጤንነት፣ አካልና ሕይወት ተስማሚ የሥራ ሁኔታ እንዲኖር፣ ትርፋቸውን <u>ብቻ</u> የሚያካብቱትን አሰሪዎች ለማስገደድ ነበር።

በተለይ ከ20ኛው ክፍለዘመን ጀምሮ በዓሉ በጎላ ሁኔታ ይከበር የነበረው ያኔ ኮሚኒስት በሚባለው ጎራ ተሰልፈው በሚገኙት አገሮች ላብ-አደሮች ነበር። ኢኮኖሚዋ በእርሻ ላይ በሚያተኩረው በአገራችን በኢትዮጵያ የሠራተኛው መደብ አባላት ቁጥር ከሕዝቡ ቁጥር አንፃር ሲወዳደር ብዙ ነው የሚባል ባይሆንም፣ አገራችን የአውሮጳን ዘመናዊነት ማስተናገድ ከጀመርንበት ከ20ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ማለትም፣ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የባቡር ሀዲድ፣ የአየር መንገድ፣ የሲሚንቶና የቃጫ ፋብሪካ፣ የለስላሳ መጠጦች፣ የሆቴሎች፣ የትምባሆ ምርትና የዘመናዊ እርሻ ግብአቶችን በመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የተሰማሩ የላብ-አደሮች ቁጥር በየዓመቱ እየጨመረ ሄዷል።

ይህ ደግሞ በአንፃሩ ላብ-አደሩ መብቶቹን ለማስከበር ማኅበር በማቋቋም በቁጥርና በድርጅት ብዛትና ጥንካሬን አግኝቶ፣ በንጉሡና በደርግ ዘመን ለመብቶቹ ያላሰለሰ ትግል

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ለማካሄድ አስችሎታል። በዚህ የትግል ጉዞውም በዋነኛነት የሚጠቀሰው ላብ-አደሩ በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን አማካይነት ታግሎ የማይናቁ ድሎችን ማስመዝገቡ ነው። ትግሉ የሠራተኛውን መብት በማስከበር ብቻ ሳይወሰን፣ በአገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያም በመሰለፍ አስተዋጽዖ ያደረገባቸው ታሪካዊ ክስተቶች በርካታ ናቸው። በመጀመሪያ፣ በንጉሡ ዘመን አገራችን በሶማሊያ ተስፋፊዎች በተወረረችበት በ1960 ዓ. ም መግቢያ ላይ፣ የሠራተኛው ማኅበር ወረራውን ለመቋቋም የሚረዳ የገንዘብ መዋጮ ከማድረጉም ባሻገር፣ ወደ ጦር ግምባር ለመዝመትም ፈቃደኝነቱን ገልጿል። በደርግ ጊዜም እንዲሁ የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች በማኅበራቸው አማካይነት ተደራጅተው የወታደራዊው መንግሥት በሕዝባዊ መንግሥት እንዲተካ ያላሰለሰ እልህ አስጨራሽና ብዙ መስዋዕትነትን ያስከፈለ ትግል አድርገዋል።

አሁንስ? በዘመነ ህወሓት የላብ-አደሩ ሁኔታ ምን ይመስላል ብሎ መጠየቁም ደግሞ ተገቢ ነው።

ማንም እንደሚገነዘበው፣ ህወሓት/ኢህአዴግ በዘር የተማከለ፣ ኢትዮጵያዊነትን የሚያሳንስና ጎሣንና ልዩነትን የሚያጎላ ፖሊሲ የሚከተል አምባገነን ቡድን መሆኑን መናገር ለቀባሪ ማርዳት ይሆናል። በዚሁ በህወሓት እኩይ ፖሊሲ የመጀመሪያ ሰለባ ከሆኑት አንዱ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር መሆኑንም ማንም የሚያውቀው ነው። ሆኖም ሠራተኛውን በዘር የመከፋፈሉ ድርጊት ህወሓት እንዳሰበው ቀላል ሆኖ አላገኘውም። የኢትዮጵያ ሠራተኞች ኢትዮጵያዊነትንና በላብ-አደርነታቸው ያሏቸውን የጋራ ጎሣ-ዘለል ችግሮች ማዕከል አድርገው የህወሓትን ጎሠኝነት በቆራጥነት መፋለም በመቀጠላቸው፣ በሠራተኛው ተቀባይነት እንዳላገኘ የተረዳው ህወሓት/ኢህአዴግ ደጋግመን ወዳየነው አምባገነናዊ አሻጥሩ ተሸጋግሮ፣ ለአንጋፋው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ተለጣፊ የሠራተኞች ማህበር ፈጠረለት። ይህን ዓይነት እኩይ ተግባሩ በሠራተኛ ማኅበር ላይ ብቻ የተወሰን ሳይሆን፣ በነፃ ሲቪክ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶችም ላይ ተደጋግሞ የታየ ተውኔት ነው።

ስለሆነም፣ በዚህ የህወሓት/ኢህአዴግ ያላሰለሰ ደባ ዛሬ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት በብዙ ችግሮች ተጠምደው ይገኛሉ። በደመወዛቸው ማነስ ምክንያት ለቤተሰባቸው ምግብ ማቅረብ የሚችሉት በጣም ጥቂቶች ሆነዋል። በተለይ ለውጭ ኩባንያዎችና ለግል አሠሪዎች የሚሠሩ ሠራተኞች የተሸራረፈ መብት ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

የመንግሥት ሠራተኞችም ቢሆኑ፣ ከነሱ ብዙ የተሻለ አቅም የላቸውም። ህወሓት/ኢህአደግ በልማት ስም የሚኩራራባቸውን መንገዶችንና ህንፃዎችን የሚሠሩ ላብ-አደሮች ሙሉ የሠራተኛ መብት እንደሌላቸው የሚታወቀው፣ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ አለመቻላቸው ነው። ይህንን ስናይ የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች ምን ያህል የመብት ረገጣ እየተደረገባቸው እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። የሠራተኛው መብቶች ደግሞ በዓለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች እነዚህን ዓለም አቀፋዊ መብቶች ተጠቅምው የመብት ጥያቄ አለማቅረባቸው ችግር ጠፍቶ ሳይሆን መብታቸው የታፈነ በመሆኑ ብቻ ነው። በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የላብ-አደሩ የድርጅት ጥንካሬ በንጉሡና በደርግ ዘመን ከነበራቸው ድርጅታዊ ጥንካሬ በእጅጉ የተዳከመ በመሆኑ ሠራተኛው መብቱን ለማስከበር በማይችልበት ሁኔታ ላይ ይገኛል። የዘንድሮውን የ2007 ዓ. ም. የሠራተኞች ቀን ስናስታውስ እነዚህን ጥቃቶች ሁሉ ታሳቢ አድርገን ነው።

ሠራተኛው ኢትዮጵያዊ ክብሩንና መብቱን ለማስከበር በህቡዕና እንዲመቹነቱም በይፋ በመደራጀት ከመታገል ሌላ ፍቱን መድሃኒት የለውም። በደርግ አፋኝ ሥርዓት ጊዜ ሕጋዊው የሠራተኛ ማኅበር ሲታገድ፣ ሠራተኛው እንደ ኢሕአፓ ካሉ ታጋይ ፓርቲዎች ጋር በማበር የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች አብዮታዊ ማኅበርን (ኢላአማ)ን መፍጠሩን ያስታውሷል። አሁንም በተለይ ወጣት ሠራተኞች ይህ ሀገራዊ ኃላፊነት የእነሱ ስለሆነ፣ ጊዜው በጠየቀው መሠረት ተደራጅተው እንደሚታገሉ ጽኑ እምነት አለን። በዚህ አጋጣሚ በ1968 ዓ. ም. የሠራተኞች ቀን ዋዜማና በዕለቱ በደርግ የተጨፈጨፉትን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኢሕአፓና የኢሕአወሊ (የወጣቱ ሊግ) አባላትን ሰማዕትነት በተመስጦ እንዘክራለን። ኢሕአፓ ዛሬም እንደ ወትሮው ከላብ-አደሩ ጋር እንደቆመ ነው።

ሠራተኛው መብቱንና ኢትዮጵያዊነቱን በትግሉ ያስከብራል!